**የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ቤተ-መጻሕፍት (DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC LIBRARY)**

**የመጨረሻ መተዳደሪያ ደንብ ማስታወቂያ**

የዲስትሪክቱ ቤተ-መጻሕፍት የቦርድ ባለአደራዎች በዲሲ ኦፊሴል ኮድ §39-105 (2011 Supp.) መሠረት ዋናው የቤተ-መጻህፍት ሃላፊ/ዳይሬክተር ሕጎችን እንዲያውጡ እና የቤተ-መጽሐፍቱን የዕለት ተዕለት ስራዎችን ለማስተዳደር ሃላፍነት ሰጥተዋቸዋል። የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ቤተ-መጻሕፍት የቦርድ ባለአደራዎች፤ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ነፃ የሆነ የህዝብ ቤተ-መጻሕፍት እና የማንበቢያ ክፍልን ለማቋቋም እና ለማሟላት በተሰጣቸው የሕግ ስልጣን በጁን 3/ 1896፣ 29 Stat. 244፣ ch. 315፣ § 5፤ ኤፕረል 1 ቀን 1926፣ 44 Stat.. 230፣ ch. 98፣ § 5፤ ማርች 3/ 1979 (የዲሲ ህግ 2-139፣ § 3205 (jjj)፣ 25 DCR 5740)፤ ሴፕቴምበር 5/ 1985 (የዲሲ ሕግ 6 – 17፣ § 2፤ 32 DCR 3582)፤ ኤፕሪል 12/ 1997 (የዲሲ ሕግ 11-259፣ § 316፤ 44 DCR 1423)፤ ኦክቶበር 21/ 1998 (በ 112 Stat. 2681 – 146፣ Pub. L.105 – 277፣ § 156 (በዲሲ ኦፊሲያል ህግ ቁጥር § 39-105 እንደተፃፈው)፣ 27 DCRR § 2.1፣ 24 DCR 11011፣ 11014 (ጁን 30/1978)፤ በ 38 DCR 1011 (ፌብሩዋሪ 1991 ዓ.ም.) በተሻሻለው የመጨረሻው መመሪያ ደንብ መሠረት §§ 810.1 እስከ 810.4 ምዕራፍ 8 (የህዝብ ቤተ-መጽሐፍት) በርዕስ 19 (መዝናኛ፣ ፓርኮች እና መናፈሻ) የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ ቤት ደንቦች (District of Columbia Municipal Regulations) (DCMR) መመሪያውን ይሰጣል።

በጃንዋሪ 27/ 2017 የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ቤተ-መጻሕፍት ዋና ዳሬክተር የአሁኑን የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ቤተ-መጻሕፍት የመተዳደሪያ ደንቦችን እንዲሻሻል በቀረበላቸው አዲስ የማሻሻያ(ዎች) ሕግ መሠረት አጽድቀውታል። የታቀደው የመተዳደሪያ ደንብ በማርች 3/2017 *በዲሲ ሬጂስተር* (*D.C. Register*) በ 64 DCR 2400 ላይ ታትሟል። ሁለቱ የተሰጡት አስተያየቶች ከተገመገሙ በኋላ ክፍል 810.6 (c) (1) መጨረሻ ላይ ሁሉንም ዓይነት ትንኮሳ የሚለውን ለማብራራት ወሲባዊ ትንኮሳን ጨምሮ የተከለከሉ ናቸው የሚል ዓረፍተ ነገር ተጨምሮበታል። ምንም ዓይነት መሠረታዊ ለውጦች አልተደረጉም።

እነዚህ ደንቦች ከጁላይ 31/ 2017 ተግባራዊ ይሆናሉ።

**ምዕራፍ 8፤ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ ቤት ደንቦች (DCMR) የህዝብ ቤተ-መጻሕፍት፤ ርዕስ 19, መዝናኛ፣ ፓርኮች እና መናፈሻ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-**

**ክፍል 810፤ ባህሪ መመሪያዎች ምላሽ ማትሪክስ የምዕራፍ 8፤ §§ 810.1 እስከ 810.4 ርዕስ 19፤ የመዝናኛ፣ ፓርኮች እና መዝናኛ የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት እንደሚከተለው ሆኖ እንዲነበብ ተሻሽሏል፡-**

## 810 የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ቤተ-መጻሕፍት የአጠቃቀም ባህሪይ መተዳደሪያ ሕግ

### 810.1 መግቢያ

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ቤተ-መጻሕፍት (DCPL) የባህሪ ሕጎች ሦስት መሠረታዊ ዋና ዓላማዎች አሉት፡- (1) የቤተ-መጻሕፍት ደንበኞችን ሙብትና ደህንነት መጠበቅ፣ (2) የሰራተኞችን ሙብቶችና ደህንነት መጠበቅ (3) የቤተ-መጻሕፍቱን ቁሳቁሶች፣ መገልገያዎች እና ንብረቶች መጠበቅ

DCPL ያለምንም አድልዎ፣ ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ ብዝበዛ ወይም የግል ሚስጢርን በለማጋለጥ ሁሉም ደንበኞች በነፃነት እና በእኩልነት ያለውን መረጃ እና የቤተ-መጻሕፍት ጥቅም እንዲጠቀሙ የሚያስላቸውን ሙብት ይደግፋል። DCPL ለሁሉም ደንበኞች ተስማሚ፣ ትህትና እና ክብር የተሞላበት አገልግሎት እና አስደሳች፣ ንፁህ እና ምቹ የሆነ አካባቢ ለማቅረብ ይተጋል።

ያለፈቃድ የቤተ-መጻሕፍት ቁሳቁሶች እና መሣሪያዎች እንዳይወጡ ወይም የቤተ-መጻህፍቱ ሰራተኞች እና ደንበኞች ጤንነት እና ደህንነት ለማስጠበቅ ሲባል DCPL፤ የደንበኞችን ንብረቶች፣ ቦርሳዎች፣ ባክፓኮዎች፣ የገበያ ቦርሳዎች፣ ብሪፍኬዞች እና ሌሎች ዕቃዎችን የመመርመር መብት ይጠብቃል።

## 810.2 ትርጉሞች እና መጠን

እነዚህ የባህሪይ ደንቦች DCPL በሚቆጣጠራቸው እና በሚያስተዳድራቸው በሁሉም ሕንፃዎች እና ግቢዎች (ሕንፃዎች እና ግቢዎች “ቅጥር ግቢዎች” ተብለውም ይጠራሉ) እንዲሁም ወደ ቅጥር ግቢዎቹ የሚገቡ እና የሚወጡ ደንበኞችን ይመለከታሉ። ከታች የተዘረዘሩት የቤተ-መጻሕፍት ባህሪይ ደንቦች ናቸው። እነዚህን ደንቦች የሚጥሱ ደንበኞች ከቅጥር ግቢዎቹ ሊወገዱና ከሁሉም የዲሲ የህዝብ ቤተ-መፃሕፍት ቅጥር ግቢዎች ከታች ለተጠቀሱት ጊዜያት ከሁሉም የቤተ-መፃሕፍት ቅጥር ግቢ በዲሲ የህዝብ ቤተ-መጻሕፍት ባለሥልጣን ሊገለሉ ይችላሉ።

## 810.3 ሕግ ማስፈጸም

የቤተ-መፃሕፍት ሠራተኛ፣ የቤተ_መፃሕፍት ፖሊስ እና/ወይም የሜትሮፖሊታን ፖሊስ ዲፓርትመንት (MPD) ባለሥልጣናት የተከለከሉ እንቅስቃሴዎችን እና ስነ ምግባሮችን ለማስቆም ጣልቃ ሊገቡ ይችላሉ። ሕግን መጣስ እስራት እና ክስ ሊያስከትል ይችላል። እነዚህን ደንቦች አለማክበር ከአንድ ቀን እስከ አምስት ዓመት ለሚሆን ጊዜ ከቤተ-መጽሐፍት ንብረት የመታገድ ማስታወቂያ ሊያሰጥ ይችላል። የመታገጃ ማስታወቂያ ከተሰጠ፤ በሁሉም የDCPL ቦታዎች ላይ ይሠራል እንዲሁም የDCPL ኮምፒውተሮች እና ሌላ መሣሪያ የመጠቀም መብት መታገድን ያጠቃልላል። እገዳው ከተደረገ፤ እገዳውን ለማስፈጸም በዲሲ የሕዝብ ቤተ-መጻሕፍት ሰራተኞች የደንበኞች ፎቶዎቻቸው ወይም ቪዲዩ ሊኖራቸው ይችላል።

## 810.4 የእገዳ ማስታወቂያዎች አስተዳደራዊ ግምገማ

a. የእገዳ ማስጠንቀቂያ ያገኙ ግለሰብ እገዳው ከሰባት (7) ቀናት በላይ ከሆነ የአስተዳደር ግምገማ መጠየቅ ይችላሉ። ይህ ጥያቄ መቅረብ ያለበት የእገዳው ማስታወቂያ ከተሰጠ በአስር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ መሆን ይኖርበታል፤ እንዲሁም በጽሑፍ ወደሚከተለው አድራሻ መላክ አለበት፡-

    Director of Public Safety
    Operations Center
    1709 Third Street, NE
    Washington, D.C. 20002

b. የሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ወይም ተወካይ የእገዳውን አስተዳደራዊ ግምገማ የመጨረሻ ውሳኔ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ይሰጣሉ። የታገዱት ግለሰብ የመጨረሻውን ውሳኔን በሚመለከት ለኮሎምቢያ ዲስትሪክት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሲቪል አስተዳደር (District of Columbia Superior Court’s Civil Division) የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

## 810.5 አግባብነት ያለው ማስተካከያ

በአካል ጉዳት ወይም በጤና ችግር ምክንያት በእነዚህ መመሪያዎች ላይ አግባብነት ያለው ለውጥን መጠየቅ የሚፈልጉ የቤተ-መጻሕፍት ደንበኞች የቤተ-መጻሕፍት ሠራተኛን ማነጋገር ወይም ወደ ADA አስተባባሪ በ 202-727-1101 መደወል ይችላሉ።

## 810.6 የባህሪይ ሕጎች

ለሕዝብ እና ለሰራተኞች ደህንነት እና ምቾት እና ለቤተ መጻህፍት አሰራር አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር የሚከተሉት ሕጎች እና ቅጣቶች ይተገበራሉ። የቤተ-መጻሕፍት ቅጥር ግቢ ውስጥ እንቅስቃሴዎች የተከለከሉ ናቸው፡-

a. <u>ምድብ አንድ ሕጎች እና ቅጣቶች</u>፡- ማንኛውም የ 9 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ ደንበኛ በቤተ-መጻሕፍት ቅጥር ግቢ ውስጥ እየለ የምድብ አንድን ሕጎች የተላለፈ ችግሩ እስኪስተካከል ድረስ ደንበኛው ከቅጥር ግቢው ይታገዳል። በዚህ ደንበኛ የሚደረጉ ተከታታይ ጥፋቶች ከታች እንደተመለከተው ግለሰቡ ከጠቅላላው የDCPL ቅጥር ግቢዎች ወዲያውኑ ይወገዳሉ እንዲሁም ማዕቀብ ይደርግባቸዋል፡-

| *ዕድሜ* | *የመጀመሪያ* | **2ኛ ጥፋት (በ30 ቀን ውስጥ)** | **3ኛ ጥፋት (በ30 ቀን ውስጥ)** | **ለ 4ኛ ጊዜ (በ30 ቀን ውስጥ)** |
|---|---|---|---|---|
| 9+ | ችግሩ እስኪስተካከል ድረስ ደንበኛው ከቅጥር ግቢው ይታገዳል | 1 ሳምንት | 1 ወር | 3 ወር |
| 0-8 | ማስጠንቀቂያ እና ለተንከባካቢ ጥቆማ ማድረግ። | | | |

1. በ DCPL ቅጥር ግቢዎች ውስጥ ወይም ደረት ከፍቶ መሄድ፣ ሸሚዝ እና ጫማ ምንጊዜም መደረግ አለበት።

2. በግልጽ በሚታይ በማንኛውም የተከለከለ ንጥረ ነገር ወይም መጠጥ ቁጥጥር ስር መሆን።

3. ከ 9” ርዝመት x 14” ስፋት x 22” ቁመት ያለፈ ቦርሳ ማምጣት። ደንበኞች በግል ሁለት ቦርሳ እንዲያመጡ ይፈቀድላቸዋል፣ ነገር ግን እያንዳንዱ ሻንጣ ከ 9” ርዝመት x 14” ስፋት x 22” ቁመት ያነሰ መሆን አለበት። የሚያመጡዋቸው ዕቃዎች ከላይ ባለው የመጠን መለኪያ ውስጥ በቀላሉ መግባት የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል። የግል ዕቃዎች ጥሎ መሄድም የተከለከለ ነው።

4. በስድስት (6) ጫማ ርቀት ላይ በሚገኝ ማንኛውም ሰው ሊስተዋል የሚችል እና/ወይም ሌሎች የቤተ-መጻሕፍት ተጠቃሚዎችን ሊረብሽ የሚችል ሽታ ያለው ማንኛውም ደንበኛ።

5. የማቅለሽለሽ ስሜት የሚፈጥር ምግብ ወይም መጠጥ መብላት ወይም መጠጣት፣ በመጥፎ ሽታ፣ ቆሻሻ ወይም ፍሳሽ ምክንያት የቤተ-መጻሕፍት አጠቃቀምን መረበሽ። መከደኛ ባለው መያዣ ውስጥ አልኮልነት የሌላቸው መጠጦች እና ምግቦች ለምግብ በተከለለ ቦታ ላይ ብቻ መጠቀም ይቻላል።

6. በቅጥር ግቢዎቹ ውስጥ መጋደም፣ መተኛት ወይም የተኙ መምሰል። የተቀመጡ ደንበኞች በቤተ-መጻሕፍቱ የተዘጋጁ መቀመጫዎችን (ወንበር፣ ሶፋ፣ ወዘተ.) መጠቀም አለባቸው። ደንበኞች በቤተ-መጻሕፍት ሰራተኛ አባል ካልተፈቀደላቸው በስተቀር ወለል፣ የእግረኛ መንገድ ላይ መቀመጥ እንዲሁም መተላለፊያዎች፣ መውጫዎች፣ መንገዶች፣ ወይም መግቢያዎችን መዝጋት አይችሉም።

7. የግል ኤሌክትሮኒክስ ያለ ጆሮ ማዳመጫ ወይም ሌሎችን በሚረብሽ ድምጽ መጠቀም።

b. <u>የምድብ ሁለት ሕጎች እና ቅጣቶች</u>፡- ማንኛውም ደንበኛ በቤተ-መጻሕፍቱ ቅጥር ግቢዎች ሆኖ የምድብ ሁለት ሕጎችን የተላለፈ በመዝገቡ ውስጥ ለ(6) ወር የሚቆይ ማስጠንቀቂያ ይሰጥዋል። በቀጣዮቹ ስድስት (6) ወራት ጊዜ ውስጥ በዚሁ ደንበኛ የሚፈጸሙ ጥፋቶች በሚከተለው መሰረት ግለሰቡ ወዲያውኑ ከማንኛውም የዲሲ የህዝብ ቤተ-መጻሕፍት ይዞታ ይወገዳል እንዲሁም ይታገዳል፡-

| ዕድሜ | **የመጀመሪያ** | **2ኛ ጥፋት (በ6 ወራት ውስጥ)** | **3ኛ ጥፋት (በ6 ወራት ውስጥ)** | **4ኛ ጥፋት (በ6 ወራት ውስጥ)** |
|---|---|---|---|---|
| 18+ | ማስጠንቀቂያ | 3 ወር | 6 ወር | 1 ዓመት |
| 13-17 | ማስጠንቀቂያ | 1 ወር | 3 ወር | 6 ወር |
| 9-12 | ማስጠንቀቂያ | 1 ሳምንት | 2 ሳምንት | 1 ወር |
| 0-8 | ማስጠንቀቂያ፣ ለተንከባካቢ እና/ወይም ለቤተ-መጻሕፍት ፖሊስ ወይም ጥቆማ ማድረግ MPD | | | |

1. በቅጥር ግቢዎቹ የፖለቲካ፣ የበጎ አድራጎት፣ ወይም የሃይማኖት ቅስቀሳዎችን ማካሄድ ወይም የድጋፍ ፊርማ ማሰባሰብ ወይም የጽሑፍ ወረቀቶችን ማሰራጨት።

2. የህዝብ ኮምፒተር መጠቀምን ጨምሮ የቤተ-መጽሐፍት አገልግሎትን ለማግኘት የሌላን ሰው የቤተ-መጻሕፍት ካርድ መጠቀም የተከለከለ ነው። እያንዳንዱ ደንበኛ የራሱን የቤተ-መጻሕፍት መጠቀም ይኖርበታል እንዲሁም እነዚህ ካርዶች ለሌላ የማይተላለፉ ናቸው፤ የቤተ-መጽሐፍት ካርድዎን ለሌላ ሰው ማዋስ የተከለከለ ነው። ይህንን ሕግን በመጣስ የተያዙ የቤተ-መጻሕፍት ካርዶች ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው በኋላ ይታገዳሉ።

3. የቤተ-መጻሕፍት ሰራተኛ ወይም ተጠቃሚ ደንበኛን በሚነካ መልኩ የግል ንብረቶችንም ሆነ ማንኛውንም ዕቃ በህንጻዎች፣ የቤተ-መጻሕፍት ዕቃዎች፣ መሳሪያዎች ላይም ሆነ አጠገብ ማስቀመጥ ወይም የግል ንብረቶችን ትቶ መሄድ።

4. ብስክሌቶችን፣ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ቁሳቁሶችን ወደ ቤተ-መጻሕፍት ሕንጻዎች ውስጥ ማምጣት በተጨማሪም መተላለፊያዎችን፣ መግቢያ በሮችን መዝጋት ነገር ግን በነዚህ ብቻ አይወሰንም። በቤተ-መጻሕፍት ቅጥር ግቢዎች ውስጥ ጥንቃቄ በጎደለው ወይም ግድየለሽ በሆነ ሁኔታ ብስክሌቶች ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን ማንቀሳቀስ።

5. በቤተ-መጻሕፍት ቅጥር ግቢዎች ውስጥ ሮለር ስኬት፣ ስኬትቦርድ፣ ሁቨርቦርድ ወይም ተመሳሳይ ነገሮችን ማንቀሳቀስ።

6. በቤተ-መጻሕፍቱ ፈቃድ በሚሰጥበት ወቅት ላይ ካልሆነ በስተቀር በቤተ-መጻሕፍቱ ሕንፃዎች ውስጥ እንስሳ ይዞ መምጣት (አገልግሎት የሚሰጡ እንስሳት ካልሆኑ በስተቀር) ወይም ያለማሰሪያ ወይም ጠባቂ በቤተ-መጻሕፍቱ ቅጥር ግቢዎች እንስሳ መተው።

7. የቤተ-መጻሕፍት መጸዳጃ ቤቶችን ለገላ መታጠቢያ፣ ጸጉር ለመላጨት፣ ጸጉር ለመታጠብ እና በአንድ የሽንት ቤት ፉርጎ ከአንድ ሰው በላይ መጠቀምን ጨምሮ (ልጆችን ወይም እርዳታ የሚያስፈልጋቸው አዋቂ ሰዎችን ለመርዳት ካልሆነ በስተቀር)፤ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን ተገቢ ባልሆነ መንገድ መጠቀም።

8. በቤተ-መጻሕፍት ውስጥ ወይም በቤተ-መጻሕፍት ቅጥር ግቢዎች ውስጥ በግልጽ በሚታይ ሁኔታ ያለቁጥጥር ወይም ጥበቃ ስምንት (8) ዓመት ወይም ከዚያ በታች የሆነው ልጅ ወይም ልጆች መተው። [እባክዎን ጠባቂ የሌላቸው ልጆች ፖሊሲ (Unattended Children Policy) የሚለውን ይመልከቱ]

9. ዕድሜያቸው (13) ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ደንበኞች ከ (12) ዓመት እና ከዚያ በታች የሆኑ ልጆችን ለማጀብ ካልሆነ በስተቀር በቤተ-መጻሕፍቱ የልጆችን ቦታ መጠቀም ወይም ለልጆች ከተቀመጡ መጻሕፍት መምረጥ አይችሉም።

10. ዕድሜያቸው (20) ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ደንበኞች እንዲሁም ዕድሜያቸው (12) ዓመት እና ከዚያ በታች የሆኑ ልጆች ዕድሜያቸው ከ (13) እስከ (19) ዓመት ያሉትን ለማጀብ ካልሆነ በስተቀር፤ ከ (13) እስከ (19) ዓመት ላሉ ወጣቶች የተዘጋጀውን ቦታ መጠቀም ወይም ለወጣቶቹ ከተቀመጡ መጻሕፍት መምረጥ አይችሉም።

11. ዕድሜያቸው (13) ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ደንበኞች ለልጆች የተመደበ ማንኛውም መጸዳጃ ቤት መጠቀም አይችሉም። የልጆች መጸዳጃ ቤቶች ዕድሜያቸው አስራ ሁለት (12) ዓመት ወይም ከዚያ በታች ለሆኑ ህጻናት እና ለእንክብካቤ ሰጪዎቻቸው ብቻ ነው።

12. ዕድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ ደንበኞች በመደበኛ የትምህርት ሰዓት ውስጥ በቤተ-መጻሕፍት ቅጥር ግቢ ውስጥ የተገኙ ተማሪዎች በቤተ-መጻሕፍት ሰራተኞች ከትምህርት ቤት ለመቅረት የተሰጣቸውን ፈቃድ ለማሳየት ሲጠየቁ ማሳየት አለባቸው።

13. የቤተ-መጻሕፍት አጠቃቀምን የሚያስተጓጉል ቆሻሻ፣ ፍሳሽ መተው ወይም አዘበራርቆ፣ ቆሻሻ ጥሎ ወይም የሆነ ነገር አፍስሶ መሄድ።

c. ምድብ ሦስት፦ የምድብ ሦስት ቅጣቶች፦ በቤተ-መጻሕፍት ቅጥር ግቢዎች ሆኖ የምድብ ሦስት ሕጎችን የሚጥስ ማንኛውም ደንበኛ በመጀመሪያ የቤተ-መጻሕፍት ሕጎች ይነገሩታል። በአንድ ዓመት ውስጥ ይህ ድንበኛ ለሚያደርጋቸው ጥፋቶች ወዲያውኑ እንዲባረር ይደረጋል እንዲሁም ከታች በተመለከተው መሰረት ከሁሉም የ DCPL ቅጥር ግቢዎች እገዳ ይደረግበታል፦

| ዕድሜ | የመጀመሪያ | 2ኛ ጥፋት (በአንድ ዓመት ውስጥ) | 3ኛ ጥፋት (በአንድ ዓመት ውስጥ) | 4ኛ ጥፋት (በአንድ ዓመት ውስጥ) |
|---|---|---|---|---|
| 18+ | 1 ወር | 3 ወር | 1 ዓመት | 2 ዓመት |
| 13-17 | 1 ሳምንት | 1 ወር | 6 ወር | 1 ዓመት |
| 9-12 | እስከ ቀኑ ማለቂያ | 1 ሳምንት | 1 ወር | 3 ወር |
| 0-8 | ማስጠንቀቂያ፣ ለተንከባካቢ እና/ወይም ለቤተ-መጻሕፍት ፖሊስ ወይም ጥቆማ ማድረግ MPD | | | |

1. የስድብ ወይም የማስፈራሪያ ቋንቋ ወይም አካላዊ እንቅስቃሴ፣ አላስፈላጊ ድምጽ የሚፈጥር ባህሪይ፣ ወይም ካለማቋረጥ ጮክ ብሎ መናገር ወይም የአካላዊ እንቅስቃሴ ረብሻ የመሳሰሉትን ጨምሮ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን መደበኛውን የቤተ-መጻሕፍት አሰራርን የሚያስተጓጉል ወይም የቤተ-መጻሕፍት ሰራተኞችን ወይም ደንበኞችን የሚረብሽ ባህሪይ ላይ መሳተፍ። ይህም ወሲባዊ ትንኮሳን ጨምሮ ሁሉንም ጥቃቶች ያካትታል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የተወሰኑ የወንጀል ጥሰቶች ወደ ምድብ አራት ሊተላለፉ ይችላሉ።

2. በሴፕቴምበር 14/ 2012 ተግባራዊ የሆነው (ዲሲ ሕግ 19-167፤ 59 ዲሲ 7820) Youth Bullying Prevention Act of 2012 (የወጣቶች የጉልበተኝነት ባህሪይ መከላከል የ2012 ሕግ) ላይ በተጠቀሰው መሰረት የጉልበተኝነት ተግባር ላይ መሳተፍ።

3. አሉታዊ፣ ስርዓት አልባ ወይም ሊጎዳ በሚችል ሁኔታ፤ ወይም በገዛ ራስ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ በሚችል ሁኔታ የቤተ-መጻሕፍት ንብረት አለአግባብ መጠቀም።

4. የቤተ-መጻሕፍት ሠራተኛ አባል ወይም የህግ አስከባሪዎች የሚሰጡትን አግባብነት ያለው መመሪያ አለመከተል።

5. በቤተ-መጻሕፍት ውስጥ ወይም በቤተ-መጻሕፍት ቅጥር ግቢ ውስጥ የኤሌክትሮኒክ ሲጋራዎችን ጨምሮ ሲጋራ ማጨስ ወይም ሌሎች የትንባሆ ምርቶችን መጠቀም።

6. *የቤተ-መጻሕፍት ኮምፒውተር የአጠቃቀም መመሪያ መጣስ።*

7. የDCPL ቅጥር ግቢዎች መግቢያ ተከልሎ ሳለ ለመግባት መሞከር (ይህ ሕግ መተላለፍ ነው)። ደንበኞች ወይም ግለሰቦች መግቢያ ተከልሎ ሳለ ወደ DCPL ቅጥር ግቢዎች ቢመለሱ በሕገ ወጥ አገባብ ሕግ DC Official Code § 22-3302 (2001 ed. & 2012 Supp.) መሰረት ሊታሰሩ እና ክስ ሊመሰረትባቸው ይችላል።

8. በቤተ-መጻሕፍት በተፈቀደ ዝግጅት ላይ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውንም የአልኮል መጠጥ ይዞ መገኘት፣ መሸጥ፣ ማሰራጨት ወይም መጠጣት።

d. <u>የምድብ አራት ቅጣቶች</u>፡- በቤተ-መጻሕፍት ቅጥር ግቢዎች ውስጥ ሆኖ የምድብ አራት ሕጎችን የሚጥስ ማንኛውም ደንበኛ ወዲያኑ እንዲወገድ ይደረግ እና በሚከተለው መሰረት ከ DCPL ቅጥር ግቢዎች ይታገዳል፡-

| ዕድሜ | እያንዳንዱ ክስተት |
|---|---|
| 18+ | 1-5 ዓመት፤ እንደ ሁኔታው እና የጥፋቱ ጥንካሬ መሰረት አግባብ ላለው የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲ ሪፖርት ይደረጋል |
| 13-17 | ከ3 ወር እስከ 1 ዓመት፤እንደ ሁኔታው እና የጥፋቱ ጥንካሬ መሰረት አግባብ ላለው የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲ ሪፖርት ይደረጋል |
| 9-12 | 1-6 ወር፤ እንደ ሁኔታው እና የጥፋቱ ጥንካሬ መሰረት አግባብ ላለው የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲ ሪፖርት ይደረጋል |
| 0-8 | ማስጠንቀቂያ፣ ለተንከባካቢ እና/ወይም ለቤተ-መጻሕፍት ፖሊስ ወይም ጥቆማ ማድረግ MPD። |

1. ማንኛውንም የፌዴራል ወይም የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ሕግ፣ ትእዛዝ፣ ኮድ ወይም ሕግን የሚጥስ ማንኛውም ድርጊት መፈጸም ወይም ለመፈጸም መሞከር።

2. በግለሰብ፣ በግለሰቦች ቡድን፣ ወይም ንብረት ላይ የተለየ አካላዊ ጉዳት ዛቻ ለማድረስ መሞከር።

3. የጾታዊ ስሜት መጨመር ወይም መርካት በሚመስል ሁኔታ በልብስ ስር የጾታ አካላትን ማሻሸትን ወይም መነካካትን ጨምሮ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን ወሲባዊ ድርጊት/ እንቅስቃሴ መፈጸም።